የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 60
ADDIS ABABA, 23th October 2024

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፫/፪ሺ፲፮
የኢትዮጵያ ደረጃዎች አዋጅ ………………ገጽ ፲፭ሺ፱፻፵፬

Content

Proclamation No. 1343/2024
Ethiopian Standards Proclamation …Page 15944

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፫/፪ሺ፲፮

## የኢትዮጵያ ደረጃዎችን አዘገጃጀት እና ማስተግበሪያ ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

በመላ ሀገሪቱ ተፈጻሚ የሚሆን የደረጃዎች ሥርዓት መዘርጋት እና ጠንካራ የደረጃ ተቋም ማቋቋም እንዲሁም የደረጃ ዝግጅትን በተመለከተ ያለውን የሥልጣንና ተግባር መደራረብ ለማስወገድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እና ወደ ውጪ ሀገር የሚላኩ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች፣ አገልግሎቶች እና ሂደቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በመቆጣጠር በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በእጽዋት እና በአካባቢ ጤናና ደህንነት፣ እንዲሁም በሀገር ጥቅም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያስከትሉ መከላከል ጠቃሚ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ደረጃዎች ትግበራን በተመለከተ በተቆጣጣሪ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅታዊ የደረጃዎችን ትግበራ በሚመለከት ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1343/2024

## A PROCLAMATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE DEVELOPMENT AND ENFORCEMENT FRAMEWORK OF ETHIOPIAN STANDARDS

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish a well-functioning Ethiopian national standards system and vibrant standard body in the country and avoid the duplication of duties and responsibilities in the process of the development of standards;

**WHEREAS,** it is necessary to regulate the quality of locally produced, import and export products, services and processes subject to Ethiopian standards in order to prevent harm on the health and safety of people, animals, plants and the environment as well as the benefit of the country;

**WHEREAS,** it is necessary to ensure the benefit of the public through creating well established coordination among the concerned regulatory bodies and establishing transparent and accountable standards development and regulatory system;



CamScanner

የኢትዮጵያ ደረጃዎች ዝግጅት እና አተገባበር ከዓለም አቀፍ አሰራር ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በማድረግ፤የኢኮኖሚ እድገት እና ማህበራዊ ለውጦችን ያገናዘበና በደረጃ ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ያጋጠሙ የአሰራር ክፍተቶችን ለመድፈን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ የሆነ የብሔራዊ ደረጃዎች ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፪) (ረ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ደረጃዎች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፵፫/፪ሺ፲፮ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/"ደረጃ" ማለት ለጋራና ተደጋጋሚ ጥቅም መሟላት ያለባቸውን የምርቶች ወይም የአገልግሎቶች መስፈርቶች፣ ባህሪያት፣ ተዛማጅ ሂደቶች ወይም የማምረቻ ዘዴዎች የሚያስቀምጥ በጋራ መግባባት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ የአስተሻሸግና የመለያ ምልክት አደራረግ መስፈርቶችን ያጠቃልላል፤

፪/ "መስፈርት" ማለት የሰዎችን፣ የእንስሳትንና የእጽዋትን ጤናና ደህንነት እንዲሁም የአካባቢ ደህንነትን ለማስጠበቅ ሲባል የሚመረቱ ምርቶች፣ የሚሰጡ አገልግሎቶች እና የሚተገበሩ ሂደቶች ማሟላት ያለባቸው ተፈላጊ ዝርዝር ሁኔታዎች ናቸው፤

**WHEREAS,** it has become necessary to harmonize the development and implementation of Ethiopian Standards in line with the International practice; to prepare a holistic national standards law taking into account the prevailing rapid economic and social transformation of the country, and considering the gaps and bottlenecks faced during the development and enforcement of Ethiopian Standards;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55/(1) and (2) (f) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Standards Proclamation''No. 1343/2024.

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:-

1/"**Standard**" means a document, developed by recognized body on the basis of consensus, that provides, for common and repeated use, rules, guidelines or characteristics for products, services or their related processes or production methods and includes packaging and labeling requirements;

2/"**Requirement**" means objectively verifiable criteria that products, Services and processes are needed to possess in order to protect the health and safety of people, animals, plants and the environment;

፫/ "የኢትዮጵያ ደረጃዎች" ማለት የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ ደረጃነት በቦርዱ አጸድቆ የሚያሳውቃቸው ደረጃዎች ናቸው፤

፬/ "የደረጃዎች ኢንስቲትዩት" ማለት ዓለም አቀፍ አሰራርን ተከትሎ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የሚያዘጋጅ ብቸኛ ብሔራዊ የደረጃ ተቋም ነው፤

፭/ "አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች" ማለት ተፈጻሚነታቸው አስገዳጅ ተብለው በቦርዱ የጸደቁ እና የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የሚያሳውቃቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚያጠቃልል ነው፤

፮/ "አስገዳጅ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች" ማለት አስገዳጅ ከሆኑ ደረጃዎች ውጪ ያሉት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ናቸው፤

፯/ "ስኪም" ማለት አንድ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሂደት የተለዩ የደረጃ መስፈርቶችንና የአሰራር ሥርዓቶችን ስለማሟላቱ የሚረጋገጥበት ዝርዝር የአሠራር መመሪያ ነው፤

፰/ "የቴክኒክ ደንብ" ማለት የምርቶችን ወይም የአገልግሎቶችን ባህርያት፣ ተያያዥ ሂደቶችን ወይም የአመራረት ዘዴዎችን እና መፈጸማቸው ግዴታ የሆነ አስተዳደራዊ ድንጋጌዎችን የያዘ ሰነድ ሆኖ በምርቶች፣ በምርት ሂደቶች ወይም በማምረቻ ዘዴዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ የቃላት አጠቃቀሞችን፣ ምልክቶችን፣ የአስተሻሸግ ወይም የመለያ አጠቃቀም መስፈርቶችን ይጨምራል፤

3/ **"Ethiopian Standards"** means any standards approved by the Board and announced by the Standards Institute as Ethiopian Stanadards;

4/ **"Standards Institute"** means an Institute which is entrusted to develop Ethiopian standrds based on International good standardization practice with the involvement of relevant bodies;

5/ **"Mandatory Ethiopian Standards"** means the requirements for products or Services whose application has been approved by the Board and announced by the Standards Institute as mandatory;

6/ **Voluntary Ethiopian Standards"** means those which are not categorized as Mandatory Ethiopian Standards;

7/ **"Scheme"** means rules, procedures and management systems which are stipulated for implementing product, service or process certification;

8/ **"Technical Regulation"** means a document which lays down product or service characteristics or their related processes and production methods, as well as administrative provisions, to which compliance is mandatory and it may also include terminologies, symbols, packaging, marking or labelling requirements as they apply to a product, process or production method;

CamScanner

፱/"ጥራት" ማለት በእያንዳንዱ ምርት፣ አገልግሎት፣ የአመራረት እና የአሰራር ሂደት ሥርዓት በቀጥታና በተዘዋዋሪ የደረጃ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው የሚገልጽ ባህሪይ ነው፤

፲/"ስልታዊ ግምገማ" ማለት ጸድቀዉ ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የአተገባበር ሁኔታ በመገምገም የመከለስ፣የማስቀጠል ወይም የመሻር ዉሳኔ እንዲሰጥ የማድረግ ሂደት ነዉ፤

፲፩/ "ምርት" ማለት በኢንዱስትሪ፣ በግብርና ወይም በባህላዊ መንገድ ተዘጋጅቶ ለንግድ የቀረበ ማንኛውም ነገር ነው፤

፲፪/ "አገልግሎት" ማለት ለተጠቃሚው ጥቅም ሲባል በተጠቃሚው ጥያቄ በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ሥራ ነው፤

፲፫/ "ሂደት" ማለት ማንኛውም የማምረት፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝ ወይም የማስወገድ ዘዴ ወይም የእነዚህ ጥምረት ነው፤

፲፬/ "የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት" ማለት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር መስማማታቸውን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ምልክት ነው፤

፲፭/ "ይሁንታ" ማለት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ማሟላታቸው ሲረጋገጥ ወደ ገበያ እንዲቀርቡ፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም ወደ ውጭ ሀገር እንዲላኩ የሚሰጥ የይለፍ ማረጋገጫ ነው፤

፲፮/ "የተስማሚነት ምዘና" ማለት በላብራቶሪ ፍተሻ፣ በሰርተፊኬሽን፣ በኢንስፔክሽን ወይም በካሊብሬሽን የደረጃ መስፈርቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

9/ **"Quality"** means the general characteristics of products, services, processes, systems and methods which describe the fulfillment level of those direct and indirect requirements;

10/ **"Systemic Review"** means a technical evaluation of implemented Ethiopian standards on the basis of their relevance as to be revised, reaffirmed or withdrawn;

11/ **"Product"** means any industrial, agricultural or indigenous product made for commercial purpose;

12/ **"Service"** means any work done for or to the benefit of, and at the request of a recipient of services and provided for remuneration;

13/ **"Process"** means any activity of production, storage, transportation or disposal or those together;

14/ **"Ethiopian Standard Mark"** means a mark given for products or services that meet the requirements of relevant Ethiopian standards;

15/ **"Permit"** means a release granted for the sell, import or export of a certain product or Service upon the verification of its compliance with the relevant Ethiopian standard requirements;

16/ **"Conformity Assessment"** means the demonstration that specified standard requirements are fulfilled by certification, inspection ,testing or calibration;

CamScanner

፲፯/ "የተስማሚነት ምዘና አካል" ማለት የሦስተኛ ወገን የተስማሚነት ምዘና ተግባራትን የሚያከናውን አካል ሆኖ የአክሬዲቴሽን ሥራን አይጨምርም፤

፲፰/ "የላቦራቶሪ ፍተሻ" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተስማሚነት ምዘና ባህሪያት መሟላት አለመሟላታቸውን ለማረጋገጥ በግልጽ ተለይቶ የተወሰነ የቅደም ተከተል ሥርዓትን ተከትሎ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

፲፱/ "ሰርተፍኬሽን" ማለት በሦስተኛ ወገን የተስማሚነት ምዘና አካላት የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፤

፳/ "አክሬዲቴሽን" ማለት የተስማሚነት ምዘና አካላትና የሥራ አመራር ሥርዓት አማካሪዎች አስቀድሞ የተወሰነ የብቃት መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በሚካሄድ ግምገማ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

፳፩/ "ኢንስፔክሽን" ማለት ማንኛውም የምርት ዲዛይን፣ ምርት፣ ሂደት ወይም የመሳሪያዎች ተከላ የተቀመጡትን ልዩ ወይም አጠቃላይ የተስማሚነት ምዘና መስፈርቶች አሟልቶ የቀረበ ስለመሆኑ በሙያዊ ምዘና የመገምገምና የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

፳፪/ "የቅድመ-ጭነት ኢንስፔክሽን" ማለት ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ሚኒስቴሩ በሚወክለው የተስማሚነት ምዘና አካል በተቀመጠው የኢትዮጵያ ወይም አለም አቀፍ መስፈርት መሰረት በመነሻ ሀገር የሚከናወን የኢንስፔክሽን አገልግሎት ነው፤

፳፫/ "ኢንስፔክተር" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የቁጥጥር ሥራ ለማከናወን በሚኒስቴሩ የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

17/ **"Conformity Assessment Body"** means a third party that performs conformity assessment activities excluding accreditation;

18/ **"Laboratory Testing"** means a test on one or more conformity assessment characteristics through the use of specified test procedures;

19/ **"Certification"** means a third party attestation related to an object of conformity assessment;

20/ **"Accreditation"** means evaluation and certification of conformity assessment bodies and management system consultants that they meet predefined competence requirements;

21/ **"Inspection"** means examination of a product design, product, process or installation and determination of its conformity with specific requirements or, on the basis of professional judgment, with general requirements;

22/ **"Pre Shipment Inspection"** means the inspection service carried out in accordance with Ethiopian or international requirements by the conformity assessment bodies delegated by the Ministry before products are imported into the country;

23/ **"Inspector"** means any professional deployed by the Ministry to perform inspection activities pursuant to this Proclamation;

CamScanner

፳፬/ **"የፋብሪካ ክትትል"** ማለት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን አሟልተው ስለመገኘታቸው ለማረጋገጥ በማምረቻ ወይም በአገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚከናወን የቁጥጥር ተግባር ነው፤

፳፭/ **"የገበያ ክትትል"** ማለት በገበያ ላይ የሚገኙ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶችን አሟልተው መገኘታቸውን እና በተከታታይነት ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን ጠብቀው መቀጠላቸውን ለማረጋገጥ በንግድ ተቋማት፣ በገበያዎች፣ በጅምላ እና በችርቻሮ መሸጫ ቦታዎች የሚከናወን የቁጥጥር ተግባር ነው፤

፳፮/ **"ፈጻሚ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን እንዲጠቀም የሚገደድ ማንኛውም ሰው ነው፤

፳፯/ **"ከባዕድ ነገር ጋር መደባለቅ"** ማለት አንድን ምርት በሙሉ ወይም በከፊል ይዘቱን በመቀየር ግርድፍ መጠኑን፣ ግዝፈቱን ወይም ክብደቱን እንዲጨምር በማድረግ ወይም ጥራቱን የተሻሻለ በማስመሰል የበለጠ ተፈላጊ እንዲመስል መሞከር ነው፤

፳፰/ **"ብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማት"** ማለት በመንግሥት ወይም በግሉ ዘርፍ የሚከናወኑ የሥነ-ልክ፣ የደረጃ ዝግጅት፣ የተስማሚነት ምዘና፣ የአክርዲቴሽን አገልግሎት እና የሕጋዊ ሥነ-ልክ ተቋማዊ፣ የቅንጅትና የአሠራር ሥርዓት በአንድነት የሚጠሩበት ስያሜ ነው፤

፳፱/ **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

24/ **"Factory Surveillance"** means a regulatory activity that is carried out at production or service delivery establishments to make sure whether products or Services meet the requirements of Mandatory Ethiopian Standards before entering to the market;

25/ **"Market Surveillance"** means a regulatory activity that is carried out at business establishments, markets, wholesaler and retailer places to ensure whether products or Services found in the market meet and maintain the relevant Mandatory Ethiopian Standard requirements;

26/ **"Implementer"** means any person who is obliged to use mandatory Ethiopian Standards pursuant to this Proclamation;

27/ **"Adulteration"** means adding any foreign substance or ingredient or substituting the content of the products in whole or in part by such other substance so as to increase their bulk, weight or strength, or make them appear better quality or greater value than they are;

28/ **"National Quality Infrastructure"** means the nomenclature to the entire institutional framework, coordination and working system whether public or private, the output of which includes metrology, standards, conformity assessment, accreditation and legal metrology;

29/ **"Ministry"** or **"Minister"** means the Ministry or Minister of Trade and Regional Integration, respectively;

CamScanner

፴/“ተቆጣጣሪ አካላት” ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ለማስፈጸም በሕግ ስልጣን የተሰጣቸው አስፈጻሚ አካላት ወይም በእነርሱ የተወከሉ አካላት ናቸው፤

፴፩/“ክልል” ማለት" በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፴፪/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፫/ በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል።

**፫.የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ በሚዘጋጁ የኢትዮጵያ ደረጃዎች፣ ደረጃ በወጣላቸው ምርቶች፣ አገልግሎቶች እና ሂደቶች እንዲሁም እነዚህን ደረጃዎችን ከማዘጋጀት፣ ከማስተግበር ወይም ከመጠቀም ጋር ግንኙነት ባለው ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ስለመቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር

**፬.መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "የደረጃዎች ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

30/ **“Regulatory Bodies”** means legally authorized executive bodies to enforce the implementation of Mandatory Ethiopian Standards or such other bodies delegated by them;

31/ **“Region”** means any state referred to under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

32/ **“Person”** means any natural or juridical person;

33/ The provisions of this Proclamation set out in masculine gender shall also apply to the feminine gender.

**3. Scope of Application**

This Proclamation shall be applicable nationwide in respect of the development of Ethiopian standards as well as products, services and processes subject to approved standards and any person engaged in the development, enforcement and application of such standards.

## PART TWO

## ESTABLISHMENT, ORGANIZATION, DUTIES AND RESPONSIBLITIES

**4. Establishment**

1/ The Institute of Ethiopian Standards (herein after the “Standards Institute”) is hereby established as an autonomous Federal Government office having its own legal personality.

2/ The Standards Institute shall be accountable to the Ministry.

CamScanner

**፭. ዋና መሥሪያ ቤት**

የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፮.ዓላማ**

የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ደረጃዎችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ የሥልጠና እና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

፪/ ዓለም ከደረሰበት መልካም ተሞክሮ ጋር የተጣጣመና ወጥነት ያለው የኢትዮጵያ የደረጃ ዝግጅት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፤

፫/ ደረጃዎችን በመጠቀም የሀገራችንን ምርቶች እና አገልግሎቶች በብሔራዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ እና ንግድን ማሳለጥ፤

፬/ ለሀገር በቀል ምርቶችና አገልግሎቶች ተገቢ የሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን በማዘጋጀት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፤

፭/ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ የልማት እንቅስቃሴ ደጋፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማጠናከር፡፡

**፯.ሥልጣንና ተግባር**

የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/የኢትዮጵያ ደረጃዎችንና ስኪሞችን የማዘጋጀት፣ በልማት ዘርፎች ውስጥ እንዲካተቱና ተግባራዊ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት እና የመደገፍ፤

፪/ በዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ክፍለ አህጉራዊ የደረጃ አዘጋጅ አካላት የሚዘጋጁ ደረጃዎች የኢትዮጵያ ደረጃዎች ሆነው እንዲጣጣሙ የማድረግ፤ የማሳተምና ተደራሽ የማድረግ፤

**5. Head Office**

The Standards Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

**6. Objective**

The Standards Institute shall have the following objectives:-

1/ To undertake study and research activities in the field of standards, provide training and consulting services;

2/ To establish a standardization system so as to develop coherent Ethiopian standards which are in line with international best practice;

3/ To enhance the competitiveness of the products and services of the country at the nationaland international level and facilitate trade through the use of standards;

4/ To develop appropriate Ethiopian standards for indigenous products and services so as to make them competitive in international market;

5/ To strengthen the situation where Ethiopian standards can be supportive of the holistic development activities of the country.

**7. Powers and Duties**

The Standards Institute shall have the powers and duties to:-

1/ Develop Ethiopian standards and schems, support and work in collaboration with the relevant executive bodies to incorporate and implement standards in all development sectors of the country;

2/ Recognize any standard published by International, Regional and Sub Regional standardization bodies as Ethiopian standard, publish and disseminate such publications;

CamScanner

፫/ ጥራትን የሚያበረታቱ ፕሮግራሞችን የመንደፍና የመተግበር፤

፬/ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የሚያዘጋጁ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን የማደራጀትና የአሰራር ሥርዓታቸውን የመወሰን፤

፭/ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ምልክቶችን ቅርጽና ይዘት የመወሰንና በምልክት የመጠቀም ፈቃድ የመስጠት፣ ምልክቱን እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸውን ሰዎች መረጃ መዝግቦ የመያዝና የመከታተል፤

፮/ የደረጃዎች፣ የተስማሚነት ምዘና አሰራሮች እና የቴክኒክ ደንቦች ብሔራዊ የመረጃ ማዕከል የማደራጀትና አገልግሎት የመስጠት፤

፯/ የጥራትና ደረጃዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ የአሰራር ሥርዓትና ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ የማድረግ፤

፰/በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር ለሚገኙ አምራቾችና አገልግሎት ሰጪዎች ደረጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ፣ ሥልጠና እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማስቻል፤

፱/ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ደረጃ ከፍ ያለና የራሳቸውን ካምፓኒ ደረጃ የማዘጋጀት አቅም እንዲያዳብሩ የቴክኒክ ድጋፍ፣ ሥልጠና እና የማማከር አገልግሎት የመስጠት፤

፲/ሸማቾችን ከመጭበርበር ለመከላከል ደረጃ የወጣላቸውን ምርቶች እና አገልግሎቶች የጥራት ዱካ ለማረጋገጥ የሚያስችል የቴክኖሎጂ የመረጃ አሰራር ሥርዓት እንዲሁም ሌሎች መተግበሪያ ዘዴዎችን የማዘጋጀትና የማስተዳደር፤

3/ Develop and implement programs necessary to encourage quality;

4/ Establish technical committees for the purpose of developing Ethiopian standards and determine their working guidelines;

5/ Determine the shape and content of Ethiopian standard mark and authorize its use, register the users in a central data base and follow up same;

6/ Establish national enquiry point and deliver services on standardization, conformity assessment guidelines and technical Regulation;

7/ Develop quality and standard awareness creation programs and working procedures and implement same;

8/ Enable domestic and foreign country based manufacturers and service providers to benefit from technology transfer through providing technical support, training and consultancy services in the implementation of standards;

9/ Build the capability of companies through technical support, training and consultancy services to develop their own excelled company standards;

10/ Develop and administer appropriate information technologies and other methods applicable to ensure whether products and services own the required quality and accurate traceability for the purpose of preventing consumers from deceptive trade practices;

፲፩/ አምራች ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት ላይ ብክለትና ብክነትን የማስወገድ ስልቶችን እንዲያዳብሩ የሥልጠና፣ የቴክኒክ ድጋፍና የምክር አገልግሎት የመስጠት፤

፲፪/ብሔራዊ የጥራት ሽልማት ሥርዓት ለመመሥረት የሚያስችል ጥናት የማካሄድ እና ሥርዓት የመዘርጋት፤

፲፫/ የደረጃዎችን ዝግጅት፣ ትግበራ፣ የሚያሳድሩትን ተፅዕኖ እና ሌሎች ተዛማች ጉዳዮች በተመለከተ የሥልጠና፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የማማከር አገልግሎቶችን የማካሄድ፤

፲፬/ ደረጃዎችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ መድረኮች ሀገሪቱን የመወከል እና ሀገሪቱ የፈረመቻቸውን ስምምነቶች አተገባበር የመከታተል፤

፲፭/ ከሀገራችን የብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማት ተቋማት እና ከባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከልማት አጋር ድርጅቶች፣ ከዓለም አቀፍ፣ አሕጉራዊ እና ብሔራዊ የደረጃ ተቋማት ጋር በትብብር የመሥራት፤

፲፮/ ለመካከለኛ እና ለአነስተኛ እንዲሁም ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት፤

፲፯/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስ እና የመከሰስ፣

፲፰/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ የማስከፈል፤

፲፱/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

11/ Provide cleaner production support to the industries through training, technical and advisory services which help them to reduce pollution and wastage during production process;

12/ Conduct research regarding national quality award system and establish the system,

13/Undertake training, research and consultancy activities on the development, application, impacts and other related issues of standards;

14/ Represent the country's interest in international forums regarding standards and follow up and support the implementation of treaties to which Ethiopia is a party;

15/ Work in collaboration with national quality infrastructure institutions and other relevant stakeholders of the country as well as relevant development partners, International, Regional and National standardization bodies;

16/ Give special support to small and medium, as well as start up businesses;

17/ Own property, enter into agreement, sue and be sued in its own name;

18/ Charge fees for the services it renders in accordance with the rate determined by the Regulation of the Council of Ministers;

19/ Carry out other related activities necessary for the attainment of its objectives.

CamScanner

**፰.<u>የደረጃዎች ኢንስቲትዩት አቋም</u>**

የደረጃዎች ኢንስቲትዩት፡-

፩/ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ") እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፱.<u>የቦርዱ አባላት</u>**

፩/ ቦርዱ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾሙ ሰብሳቢውን ጨምሮ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ፣ከሸማች፣ ከግል ዘርፍ ፣ከተቆጣጣሪ አካላት እና ከአካዳሚያ የተውጣጡ ከአስራ አንድ ያልበለጡ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ጸሐፊ ይሆናል፡፡

**፲. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የአጭር እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ እንዲሁም ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ለመንግሥት ከመቅረቡ በፊት ይገመግማል፣ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፪/ ከአገልግሎት ክፍያና ከሌሎች ምንጮች የሚገኘውን የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ተጨማሪ በጀት መርምሮ የሀገሪቱን የፋይናንስ ሕጎች መሠረታዊ መርሆች በመከተል ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፫/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን ሥራዎች አፈጻጸም ይመራል፣ ይከታተላል ይገመግማል፤

**8. <u>Organization of the Standards Institute</u>**

The Standards Institute shall have:-

1/ Ethiopian Standards Board (hereinafter the "Board");

2/ A Director General and Deputy Director Generals, as necessary; and

3/ The necessary staff.

**9. <u>Members of the Board</u>**

1/ The Board shall consist not more than eleven members including the chairperson, drawn from the appropriate Government organs and other bodies including consumers, private sectors, regulators and acadamia appointed by the Government upon the recommendation of the Minister.

2/ The Director General of the Standards Institute shall be member and secretary of the Board.

**10. <u>Powers and Duties of the Board</u>**

The Board shall have the powers and duties to:-

1/ Evaluate the short and long term plans as well as annual plans, work programs and budgets of the Standards Institute before submission to the Government and follow up their implementation upon approval;

2/ Evaluate and approve the additional budget of the Standards Institute earned from service charges and other sources following the basic principles of the financial laws of the country and follow up its implementation;

3/Direct, oversee and evaluate the performance of the Standards Institute;

CamScanner

፬/የሲቪል ሰርቪስ መሠረታዊ መርሆችን በመከተል የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን ሠራተኞች፣ አሰልጣኞችና አማካሪዎች የቅጥርና አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፣ ደመወዝና አበላቸውንም ይወስናል፣

፭/በቴክኒክ ኮሚቴዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡ አስገዳጅ የሆኑ እና አስገዳጅ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ገምግሞ ያፀድቃል፣

፮ በተለያዩ መስኮች ለሚዘጋጁ ደረጃዎች የዘርፍ አማካሪዎችን ያዋቅራል፣

፯/በደረጃዎች ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር በሚቀርቡለት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

## ፲፩.የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፪/ ከቦርዱ አባላት ሁለት ሦስተኛ አባላት በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ያልፋሉ።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፪.የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን

፩/ የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።

፪/ማንኛውም የቦርድ አባል ከቦርድ አባልነቱ ሊነሳ የሚችለው፡-

4/ Issue Directive governing the employment and administration of employees, trainers and consultants of the Standards Institute and determine their salary and benefits following the basic principles of the civil service laws of the country;

5/ Examine and approve voluntary and mandatory Ethiopian standards proposed by technical committees;

6/ Establish sectorial advisory committees necessary for the development of standards in different fields;

7/ Decide on such matters as may be submitted to it by the Director General of the Standards Institute.

## 11. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet every three months; provided, however, that extraordinary meeting may be held at any time when called by the chairperson.

2/ There shall be a quorum when 2/3 votes of the members of the Board are present at any meeting.

3/ Any decisions of the Board shall be passed by 2/3 votes of members present at a meeting.

4/ The Board may, without prejudice to the provisions of this Article, adopt its own rules of procedures governing the conduct of meetings.

## 12. Term of Office

1/ The term of office for the members of the Board shall be five years.

2/ Any member of the Board may be removed from the Board when he:-

CamScanner

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን የሥነ ምግባር መመሪያ የጣሰ እንደሆነ፤

ለ) በተደጋጋሚ ከቦርድ ስብሰባ ያለበቂ ምክንያት የሚቀር ከሆነ፤

ሐ)ብቃትና ችሎታ የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ፤

መ) በአእምሮ ወይም በአካላዊ ሕመም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ፤ ወይም

ሠ) የወከለውን ተቋም ከለቀቀ ነው::

፲፫.<u>የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ለደረጃዎች ኢንስቲትዩት የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን ሠራተኞች፣ አሰልጣኞችና አማካሪዎች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን የአጭርና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂክ እቅድ እንዲሁም ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ እና ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለደረጃዎች ኢንስቲትዩት የተመደበው በጀትና ሀብት በአግባቡ ወጪ መደረጉን እና ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

(a) Has violated the code of conduct issued pursuant to this Proclamation;

(b) Has a repeated unacceptable absence to the meetings;

(c) Has shown manifested incompetence and inefficiency;

(d) Can no longer carry out his responsibilities on account of mental or physical illness; or

(e) Has left the Institution he represented.

13.<u>Powers and Duties of the Director General</u>

1/ The Director General shall be the chief executive officer and shall direct and administer the activities of the Standards Institute.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:-

a) Exercise the powers and duties of the Standards Institute specified under Article 7 of this Proclamation;

b) Recruit and administer employees, trainers and consultants of the Standards Institute on the basis of Directive issued by the Board;

c) Prepare and submit to the Board and the Ministry short and long term strategic plans as well as annual plans, work programs and budgets of the Standards Institute and implement same upon approval;

d) Effect expenditures and ensure its implementation in accordance with the approved budget of the Standards Institute;

CamScanner

ሠ)የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ እና ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን ይወክላል፤

ሰ)ለሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌሎች የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

**፲፬.የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጠው አጠቃላይ የሥራ መመሪያ መሠረት በሥሩ የተመደቡለትን የሥራ ዘርፍ ይመራል፤ ያስተባብራል፤

፪/የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፤

፫/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፬/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ካሉና ዋና ዳይሬክተሩ በተለየ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶ ይሰራል።

**፲፭.የገቢ ምንጮች**

፩/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ገቢ ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፦

ሀ) ከሚሰበስበው የአገልግሎት ክፍያ፤

ለ) በመንግሥት ከሚመደብ የበጀት ድጋፍ፤

ሐ) ከሌሎች የድጋፍና የገቢ ምንጮች።

e) Prepare the performance and financial reports of the Standards Institute and submit same to the Board and the Ministry;

f) Represent the Standards Institute in its dealings with third parties;

g) Delegate part of his powers and duties to other officers and staff to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Standards Institute.

**14. Powers and Duties of the Deputy Director General**

The Deputy Director General shall have the powers and duties to:

1/ Direct and coordinate sectors and divisions under him as per the general direction of the Director General;

2/ Assist the Director General by planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Standards Institute;

3/ Perform other duties assigned to him by the Director General;

4/ Act on behalf of the Director General in his absence; where there are more than one Deputy Director Generals and no specific delegation has been given by the Director General, the Deputy Director General who is senior by appointment shall act on behalf of the Director General.

**15. Source of Income**

1/The Standards Institute shall have the following sources of income:

a. Fees collected from the service it provides;

b. Budgetary support of the Government;

c. Income earned from different supports and other sources.

CamScanner

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚያገኘውን ገቢ በቦርዱ እያስጸደቀ ዓላማውን ለማስፈጸም እንዲጠቀምበት ተፈቅዷል።

**፲፮. የሒሳብ መዛግብት**

፩/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የሒሳብና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ክፍል ሦስት

## የኢትዮጵያ ደረጃዎች አዘገጃጀት ሥርዓት

**፲፯/ ደረጃ የማውጣት ሥልጣን**

፩/በአገሪቷ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማዘጋጀት፣የማሻሻል እና የማስራጨት ሥልጣን ያለው ዋነኛው አካል የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ይሆናል።

፪/ የኢትዮጵያ ደረጃ ዝግጅትን አስመልክቶ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ከፍተኛው አካል እንደመሆኑ መጠን የአገሪቷን ምርቶች፣አገልግሎቶች ወይም የተለያዩ ሥርዓቶች እንዲሁም የአሰራር ሥርዓቶች እና የአፈታተሽ ስልቶች ላይ ደረጃዎችን በማዘጋጀት እና በማሳተም ለህዝቡ እንዲቀርቡ የሚያደርገው ብቸኛው መንግስታዊ አካል ነው።

፫/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩትን ሕጋዊ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውም ሰው ወይም አካል የኢትዮጵያ ደረጃ አዘጋጅቶ ማቅረብ አይችልም።

2/ The Standards Institute is allowed to utilize the income specified under Sub-Article (1) of this Article to achieve its objectives upon the approval of the Board.

**16. Books of Accounts**

1/ The Standards Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Standards Institute shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

## PART THREE

## THE DEVELOPMENT SYSTEM OF ETHIOPIAN STANDARDS

**17. Authority to Standardization**

1/ The Standards Institute shall be the peak national standards body for the development, maintenance and promotion of Ethiopian Standards.

2/ The Standards Institute, in its capacity as the peak national standards body, shall be the sole Government body to develop, establish and publish national standards for products, service or systems, code of practice, and methods of tests.

3/ No person shall issue a document that create, or may create the impression that it is or contain an Ethiopian Standards without the official permission of the Standards Institute.

CamScanner

**፲፰. <u>የኢትዮጵያ ደረጃዎች ዝግጅት</u>**

፩/ አዲስ የኢትዮጵያ ደረጃዎች አለም አቀፍ፣ አህጉራዊ ወይም የሌሎች ሃገራት ደረጃዎችን ቀጥታ በመውሰድ፣ በማጣጣም ወይም እንደማጣቀሻ በመውሰድ ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

፪/ የሀገር በቀል ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ደረጃዎች የሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር ውጤቶችን በመጠቀም የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ደረጃዎች አስገዳጅ ሆነው የሚጸድቁት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት የተጽዕኖ ግምገማ ከተደረገባቸው በኋላ ነው፡-

ሀ) የሰዎች ጤንነት እና ደህንነት፤

ለ) የእንስሳት እና የእፅዋት ጤንነት እና ደህንነት፤

ሐ) የአካባቢ ጥበቃ፤

መ)የንግድ ማጭበርበር ተግባራትን መከላከል፤ እና

ሠ) የብሔራዊ ደህንነት ፍላጎት፡፡

**፲፱.<u>የአዲስ ደረጃ ዝግጅት ጥያቄ አቀራረብ</u>**

፩/ አዲስ የኢትዮጵያ ደረጃ እንዲዘጋጅ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና የተወሰነውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈል ለደረጃዎች ኢንስቲትዩት በጽሁፍ ማመልከት ይችላል፡፡

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በቀረበው የደረጃ ዝግጅት ጥያቄ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከቱት መሥፈርቶች መሠረት የአስፈላጊነት እና የተጽእኖ ግምገማ ተካሂዶ የውሳኔ ሐሳብ እንዲቀርብ ጉዳዩን ለቴክኒክ ኮሚቴ ይመራዋል፡፡

**18. <u>Development of Ethiopian Standards</u>**

1/New Ethiopian standards may be developed by adopting, adapting or making reference to International, Regional or National standard bodies of other countries.

2/ Standards for indigenous products and services shall be developed based on scientific studies and research findings.

3/ Ethiopian standards shall be declared as mandatory on the basis of impact assessment in accordance with the following requirements:-

a) Human health and safety;

b) Animal and plant life and safety;

c) Protection of the environment;

d) Prevention of deceptive trade practices; and

e) National security interest.

**19. <u>Initiation and Proposal of New Standards</u>**

1/ A new standard proposal may be initiated by any interested person and be submitted to the Standards Institute in writing upon filling the required form and paying the prescribed fees.

2/ The Standards Institute shall refer the initiation request to the relevant technical committee and require coming up with its recommendation after conducting the necessary impact assessment based on the requirements specified under Article 18 (3) of this Proclamation.

CamScanner

፫/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጥያቄውን የተቀበለው መሆኑን ወይም ያልተቀበለው ከሆነ ምክንያቱን ጭምር በመግለጽ ማመልከቻው በቀረበለት በሰላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

፬/ አመልካቹ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በሰጠው ምላሽ ካልተስማማ ውሳኔው በደረሰው በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታዉን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡

፭/ ቦርዱ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የደረጃ ዝግጅት ጥያቄ የሚቀርብበት እና የሚስተናገድበት ዝርዝር አሠራር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳.ስለቴክኒክ ኮሚቴዎች**

፩/ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ከመንግሥታዊ ተቋማት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከግል ድርጅቶች እና ከሲቪል ማህበራት የተወጣጡ ይሆናሉ፡፡

፪/ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ተገቢውን ሐሳባቸውን ካንጸባረቁ በኋላ በረቂቅ ደረጃው ላይ በጋራ ስምምነት ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በረቂቅ ደረጃው ላይ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ካልተቻለ በቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

፬/ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ዝርዝር አሰራር በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ The Standards Institute shall notify the applicant in writing the acceptance or rejection of the request including its reasons within thirty working days from the receipt of the application.

4/ The applicant may lodge his complaint to the Board within fifteen days from the receipt of the decision if he is not satisfied with the decision of the Standards Institute.

5/ The Board shall examine the complaint and render a final decision within thirty days.

6/ Without prejudice to the provisions of this Article, the detail procedures for the request of standard development shall be governed by Directive issued hereunder.

**20. Technical Committees**

1/ Members of Technical Committees are drawn from government institutions, non-governmental organizations, private undertakings and civil societies.

2/ Consensus shall be reached on the proposed standards based on fair reflection of opinion by members of the Technical Committees.

3/ Decisions of Technical Committees shall be made by two third votes of the members if consensus cannot be reached on the proposed standards pursuant to sub-article (2) of this Article.

4/ The detail working procedures of technical committees shall be determined by Directive issued hereunder.

CamScanner

## ፳፩.የሕዝብ አስተያየት ስለመቀበል

፩/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በቴክኒክ ኮሚቴዎች የተዘጋጀ ማንኛውም የደረጃ ረቂቅ በድረ-ገጹ ላይ ቢያንስ ለስልሳ ቀናት ለሕዝብ አስተያየት ክፍት ሆኖ እንዲቆይ ማድረግ አለበት፡፡

፪/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይና አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የስልሳ ቀናት ጊዜው በቦርዱ ውሳኔ ሊያጥር ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከህዝብ የተሰበሰቡ አስተያየቶች ለሚመለከተው የቴክኒክ ኮሚቴ ቀርበው ሙያዊ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

፬/ የቴክኒክ ኮሚቴዎች የተጽዕኖ ግምገማን፣ የተቆጣጣሪ አካላት ምክክርን እና የሕዝብ አስተያየትን መሠረት በማድረግ አስገዳጅ የሆኑ እና አስገዳጅ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ረቂቅ ለቦርዱ ውሳኔ ያቀርባሉ፡፡

## ፳፪. ደረጃዎችን ስለማጽደቅ

ቦርዱ በቴክኒክ ኮሚቴዎች የቀረቡለትን አስገዳጅ የሆኑ እና አስገዳጅ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ገምግሞ ያጸድቃል፡፡

## ፳፫. የደረጃዎች ሕትመትና ማስተዋወቅ

፩/የደረጃዎች ኢንስቲትዩት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ስለመጽደቃቸው ከጸደቁበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በሀገሪቱ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና በድረ-ገጹ ለሕዝብ ማስተዋወቅ አለበት፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ከጸደቁበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ የሥራ ቀናት ውስጥ በደረጃዎች ኢንስቲትዩት መታተም ይኖርባቸዋል፡፡

## 21. Public Comment Hearing Period

1/ The Standards Institute shall publicize any proposed standards for public comment on its website for the period not less than sixty days.

2/Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, in the case of emergency, the Board may decide the publication of any proposed standards for public comment on website for the period less than sixty days.

3/ Public comments gathered pursuant to Sub-Article (1) of this article shall be submitted to the relevant technical committee for its technical decision.

4/ The Technical Committees shall submit draft voluntary and mandatory Ethiopian standards to the decision of the Board based on Systemic Review, the consultation of regulatory bodies and public comments.

## 22. Standard Approval

The Board shall examine and approve mandatory and voluntary Ethiopian standards proposed by the technical committees.

## 23. Publication and Notification of Standards

1/ The Standards Institute shall publicize the approval of Ethiopian standards by a newspaper having wider circulation in the country and on its website within fifteen working days from their approval.

2/ The Standards Institute shall publish Ethiopian standards within thirty working days from their approval.

፫/ማንኛውም ሰው የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል የጸደቁ ደረጃዎችን ሕትመት ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት መውሰድ ይችላል፡፡

**፳፬. ስልታዊ ግምገማ**

፩/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በየአምስት ዓመቱ ወይም በሚያደርገው የተጽዕኖ ግምገማ ግኝት ወይም ከተቆጣጣሪ አካላት በጽሁፍ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት በጸደቁ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ላይ ስልታዊ ግምገማ ያደርጋል፡፡

፪/ ስልታዊ ግምገማ የሚደረገው በትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን፣ ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ ሀገራዊ ፍላጎቶችን እና አለም አቀፍ የገበያ ውድድርን መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

፫/ በሚደረገው ስልታዊ ግምገማ መሰረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ደረጃ ሊከለስ ፣ ባለበት ሊቀጥል ወይም ሊሻር ይችላል፤ ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት
## የኢትዮጵያ ደረጃዎች የምልክት አስተዳደር

**፳፭.ስለደረጃ ምልክት ፈቃድ አሰጣጥ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት የጸና ፈቃድ ሳያገኝ በማንኛውም ምርት ወይም አገልግሎት ላይ የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክትን ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የሚያገኘው በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እና በምልክት አሰጣጥ ስኪም መሰረት ምርቱ ወይም አገልግሎቱ ተገቢውን የደረጃ መስፈርት ማሟላቱን እውቅና ባለው የተስማሚነት ምዘና አካል ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ነው፡፡

3/ Any person can seek and obtain from the Standards Institute the publication of approved Ethiopian standards upon the payment of the prescribed fees.

**24. Systemic Review**

1/ The Standards Institute shall carry out systemic review on approved Ethiopian Standards every five years or upon findings of impact assessment or based on a written request of any regulatory body.

2/ Systemic Review shall be carried out on the basis of practical problems, updated technology, national needs and competitiveness on international market.

3/ Any Ethiopian standards may be revised, reaffirmed or withdrawn based on systemic review; Details shall be determined by Directive issued hereunder.

## PART FOUR
## ADMINSTRATION OF ETHIOPIAN STANDARDS MARKS

**25. Eligibility to a Standard Mark**

1/No person shall use Ethiopian standard mark on any product or service without having a valid authorization from the Standards Institute.

2/A person shall be authorized to use Ethiopian standard mark upon ascertaining the conformity of the product or the service to the relevant Ethiopian standard requirements by an accredited conformity assessment body in accordance with this Proclamation, Regulation and Directive issued hereunder and the certification

CamScanner

፫/ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የሚያመርት፣ ወደ ዉጭ ሀገር የሚልክ፣ ከውጭ ሀገር የሚያስመጣ ወይም በሀገር ዉስጥ ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ደረጃዎችን ስለማሟላቱ ዕውቅና ካለው የተስማሚነት ምዘና አካል የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማቅረብ እና አስገዳጅ የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፬/ አስገዳጅ ደረጃ ላልወጣላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የደረጃ ምልክት ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይወሰናል፡፡

**፳፮. የደረጃ ምልክት አጠቃቀም**

፩/ የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ምልክቱን መጠቀም የሚችለው ፈቃድ ለተሰጠበት ምርት ወይም አገልግሎት ብቻ ነው፡፡

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት ለመጠቀም ፈቃድ የተሰጣቸውን ሰዎች ለመመዝገብ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

**፳፯. የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት ፈቃድን ስለማደስ፣ ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ**

፩/ በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ ምርቶች ወይም ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚሰጥ የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት የመጠቀም ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ለማንኛውም ሰው የሰጠውን የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያግድ ይችላል፡-

scheme.

3/ Any person who produces, exports, imports or supplies to the market any product or service subject to Mandatory Ethiopian Standards is required to hold a conformity certificate and to use a mandatory Standards mark.

4/ The requirements for the authorization of Ethiopian standards mark for voluntary standards of products or services shall be determined by the Regulation and Directive issued hereunder.

**26. Use of Standard Mark**

1/ Any person authorized to use Ethiopian standard mark shall use the mark only for those products or services specified in the permit.

2/ The Standards Institute shall establish a register of persons authorized to use Ethiopian standard mark.

**27. Renewal Suspension or Revocation of Standard Mark**

1/ Any Ethiopian standard mark used for local products or services shall be renewed every year.

2/ The Standards Institute shall suspend the authorization of Ethiopian standard mark where:

ሀ) ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የተቀመጡትን መስፈርቶች የጣሰ ከሆነ፤

ለ) የሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል በጥራት መጓደል ምክንያት በምርቱ ወይም በአገልግሎቱ ላይ እገዳ የጣለበት ከሆነ፤

ሐ) የተስማሚነት ምዘና አካል ለባለፈቃዱ የሰጠውን የምርት ወይም የአገልግሎት ጥራት የምስክር ወረቀት በማገድ ለደረጃዎች ኢንስቲትዩት ካሳወቀ፤

መ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ከተሰጠው ዓላማ ውጪ ሲገለገልበት ከተገኘ፤ ወይም

ሠ) ፈቃዱ የተሰጠው ወይም የታደሰው በሀሰተኛ ማስረጃ ተመሥርቶ መሆኑ ከተረጋገጠ፡፡

፫/ ፈቃዱ የታገደበት ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለዕገዳው ምክንያት የሆነውን ነገር አስተካክሎ ካልቀረበ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ፈቃዱን ይሰርዘዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት ፈቃድ አሰጣጥ፣ አጠቃቀም፣ እድሳት፣ እገዳ፣ ስረዛና የክፍያ ሁኔታ ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይወሰናል፡፡

a) The holder violates those requirements specified in this Proclamation, regulations or Directive issued hereunder;

b) The relevant regulator suspended the product or the service for the reason of substandard quality;

c) The conformity assessment body notified the Standards Institute the suspension of the certificate of conformity issued for the product or the service of the holder;

d) The permit is used by the holder for an unauthorized purpose; or

e) It is verified that the permit was issued or renewed based on falsified document.

3/ The Standards Institute shall revoke the suspended authorization of Ethiopian Standard Mark unless the people rectify the reason for its suspension within the period specified in the Regulation issued hereunder.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the detail conditions for the authorization, use, renewal, suspension and revocation of Ethiopian Standard Mark shall be prescribed by Regulation and Directive issued hereunder.

CamScanner

## ክፍል አምስት

## አስገዳጅ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የማስተግበሪያ ሥርዓት

**፳፰. ደረጃዎችን በሕግ ስለማካተት**

፩/ አስገዳጅ ያልሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች በሚወጡ ህጎች ውስጥ ሲካተቱ አስገዳጅ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ አስፈጻሚ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ለመተግበር የሚከተሉትን አማራጮች መከተል ይችላሉ፡-

ሀ) ደረጃውን በሙሉ ወይም በከፊል ማጣቀስ፤ ወይም

ለ) የደረጃውን ቁጥርና ርዕስ መግለጽ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በሕግ የተካተቱትን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ደረጃዎቹን ስለማሟላቱ ዕውቅና ካለው የተስማሚነት ምዘና አካል ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

**፳፱. ደረጃዎችን በግዢ ማእቀፍ ውስጥ ስለማካተት**

፩/ አስገዳጅ ያልሆኑ ደረጃዎችን በከፊል ወይም በሙሉ በማጣቀስ ወይም ርእስና ቁጥራቸውን በመግለጽ በግዢ የጨረታ ሰነድ ውስጥ ሲካተቱ አስገዳጅ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በግዥ ማእቀፍ ውስጥ የተካተቱትን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ደረጃዎቹን ስለማሟላቱ ዕውቅና ካለው የተስማሚነት ምዘና አካል ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

## PART FIVE

## ENFORCEMENT MECHANISM OF VOLUNTARY ETHIOPIAN STANDARDS

**28. Referencing and Incorporation of Standards in Laws**

1/ Voluntary Ethiopian standards shall have a mandatory application when they become part of any law.

2/ Executive bodies may have the following options to enforce standards in the manner specified under sub-article (1) of this Article:-

a) By referencing all or part of the Standards; or

b) By referencing the number and title of the standards.

3/ Any person who supplies products or services specified under Sub-Article (2) of this Article is required to hold a conformity certificate from a recognized conformity assessment body.

**29. Integrating Standards in Procurement Packages**

1/ Voluntary Ethiopian standards shall be mandatorily enforced if integrated in procurement bids either by reference or direct integration.

2/ Any person who supplies products or services integrated in procurement bids in accordance with sub-article (1) of this Article is required to hold a conformity certificate from a recognized conformity assessment body.

CamScanner

## ክፍል ስድስት

## የአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የማስተግበሪያ ሥርዓት

### ፴.የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ አግባብ ባለው ሕግ ለሌሎች አስፈጻሚ አካላት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ይቆጣጠራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች እንዲዘጋጁ ወይም እንዲከለሱ ለደረጃዎች ኢንስቲትዩት ሐሳብ ያቀርባል፣ ሲጸድቁም ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ጊዜ በድረ-ገጹ እና በሀገሪቱ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ለሕዝብ ያሳውቃል፤

ለ) የገቢ ንግድ እቃዎችን በዚህ አዋጅ በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት ገምግሞ ይመዘግባል፤

ሐ)አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የወጣላቸው ምርቶች እና አገልግሎቶች ለገበያ ከመቅረባቸው፣ ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው ወይም ወደ ውጪ ሀገር ከመላካቸው በፊት አስገዳጅ ደረጃዎችን ማሟላታቸውን አረጋግጦ ይሁንታ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

መ)የኢንስፔክሽን ድግግሞሹ የአደጋ ስጋትን መሠረት ባደረገ ሁኔታ የፋብሪካና የገበያ ክትትል እንዲሁም የገቢና ወጪ ዕቃዎች ጥራት ቁጥጥር ያካሂዳል፤

## PART SIX

## ENFORCEMENT OF MANDATORY ETHIOPIAN STANDARDS

### 30. Powers and Duties of the Ministry

1. Without prejudice to powers given to other executive bodies in accordance with the relevant laws, the Ministry shall regulate products and services subject to mandatory Ethiopian standards.

2. Without prejudice to the generality of the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Ministry shall:-

a)Propose the development or revision of mandatory Ethiopian standards to the Standards Institute and upon approval notify their effectiveness to the public on its website and a newspaper having wider circulation in the country;

b) Evaluate and register imported commercial products based on the applicable requirements specified in the Regulation and Directive issued hereunder;

c) Issue permit to products and Services subject to mandatory Ethiopian standards upon verifying the fulfillment of quality requirements before being supplied to the market, entering and leaving the country and control their compliance accordingly;

d) Conduct factory and market surveillance as well as quality inspection of import and export products on risk basis;

CamScanner

ሠ)አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የወጣላቸውን ምርቶች ኢንስፔክሽን ያካሂዳል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ናሙና በነጻ ይወስዳል፣ በላቦራቶሪ ያስፈትሻል፣ በውጤቱ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

ረ)እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በኢትዮጵያ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ አለም አቀፍ ደረጃዎች መሰረት በተመረጡ እውቅና ባላቸው የሀገር ውስጥ ወይም ዓለም አቀፍ የተስማሚነት ምዘና አካላት ከመነሻ ሀገራት እየተረጋገጡ እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል የቅድመ ጭነት ኢንስፔክሽን አገልግሎት ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሰ)አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ሳያሟሉ የተሠራጩ ምርቶች እንዲሰበሰቡ እና አገልግሎቶች እንዲቋረጡ ያደርጋል፤

ሸ) እንደ አስፈላጊነቱ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የኢትዮጵያ አስገዳጅ ደረጃዎችን ስለማሟላታቸው ከተስማሚነት ምዘና አካላት የሚሰጡ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶችን በመቀበል ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤

ቀ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የወጣላቸው ምርቶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሲያበቃ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ጥቅም ላይ የማይውሉ ሆነው ሲገኙ አግባብ ካለው የመንግሥት አካል ጋር በመተባበር በባለቤቱ ወጭ እንዲወገዱ ያደርጋል፤

በ) በሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት ቁጥጥር የሚደረግባቸው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያስተባብራል፤

e) Undertake inspection ,take sample free of charge, cause the conduct of Laboratory Test on products subjects to mandatory Ethiopian Standards and render decision based on the result;

f) Implement, where necessary, pre-shipment Inspection service of import products in the countries of origin by national or international Conformity Assessment Bodies in accordance with the recognized Ethiopian or other similar international standards;

g) Order the recall of market distributed products and the termination of Services that failed to meet the requirements of mandatory Ethiopian standards;

h) Render an appropriate decision, as necessary, on the standards of products or Services upon the receipt of a conformity certificate issued by the recognized conformity assessment bodies;

i) Cause the disposal of products subject to mandatory Ethiopian standards in collaboration with the relevant bodies and at the expense of the owner when they expire or when they are confirmed to be unfit for use pursuant to this Proclamation;

j) Coordinate other regulatory bodies in order to facilitate the coherent enforcement of mandatory Ethiopian standards under their jurisdiction;

CamScanner

ተ) የቴክኒክ ደንቦች አዘገጃጀት ዓለም አቀፍ የንግድ አሰራርን የተከተለ እንዲሆን ለማስቻል ከሚመለከታቸው የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የቴክኒክ ደንቦችን የሚመለከቱ የጋራ ስምምነቶችን ይፈራረማል፣ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

ቸ) የሀገሪቱን የቴክኒክ ደንቦች የሚመለከቱ መረጃዎችን አደራጅቶ ይይዛል፣ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ለተለያዩ ሀገራት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ያሳውቃል፤

ኀ) ይህን አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ለማስተግበር ኢንስፔክተሮችን ይመድባል።

**፴፩.የፈጻሚ መብቶችና ግዴታዎች**

፩/ማንኛውም ፈጻሚ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ማንኛውም ኢንስፔክተር በመንግሥት የሥራ ሰአትም ሆነ ከሥራ ሰዓት ውጭ ለኢንስፔክሽን ስራ ወደ ፋብሪካ ወይም ወደ ገበያ ሲመጣ ኢንስፔክተር ስለመሆኑ የሚገልፅ ሚኒስቴሩ የሰጠውን የመታወቂያ ወረቀት እና ደብዳቤ የመጠየቅ፣ የማየትና የማረጋገጥ፤

ለ) የኢንስፔክሽን ስራውን በተመለከተ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ከኢንስፔክተሩ የመጠየቅና የማግኘት፤

ሐ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ካላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ጥራት ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ዓይነት ጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ ለሚኒስቴሩ የማቅረብና ምላሽ የማግኘት፤

k) Work in collaboration with the concerned national and international institutions to ensure that technical regulations are developed in line with international trade practices; Sign with different countries mutual agreements related to technical Regulation; implement same upon approval and oversee their implementation;

l) Organize and maintain a national database of technical Regulation and give notification services to other countries and international organizations in accordance with international agreements;

m) Deploy inspectors who perform Inspection activities for the implementation of this Proclamation, Regulation and Directive issued hereunder.

**31. Rights and Obligations of the Implementer**

1/ Any Implementer shall have the right to:-

a) Require and verify the identification card and an authorization letter issued by the Ministry when the inspector is assigned on duty in the factory or market establishment for Inspection during and out of working hours;

b) Seek and receive from the inspector any information concerning the inspection;

c) Reveal any information, lodge complaints and get the necessary response from the Ministry regarding the quality of products or services subject to mandatory Ethiopian standards;

መ) ተገቢ ሥነ ምግባር የተላበሰ፣ ከአድሎዎ የፀዳ እና ቀልጣፋ አገልግሎት ከሚኒስቴሩ የማግኘት፡፡

፪/ማንኛውም ፈጻሚ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ)ኢንስፔክተሩ በመንግሥት የሥራ ሰአትም ሆነ ከሥራ ሰአት ውጭ ሚኒስቴሩ የሰጠውን የመታወቂያ ወረቀት እና ደብዳቤ በማሳየት ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በንግድ ድርጅቱ ውስጥ እንዲገባ፣ ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርግ፣ ከማምረቻ፣ ከማከማቻ ወይም ከማጓጓዣዎች ላይ የምርት ናሙና ያለክፍያ እንዲወስድ እና ማናቸውንም ከኢንስፔክሽን ሥራው ጋር የተያያዙ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲያገኝ የመፍቀድ፤

ለ)አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወዲያውኑ የመስጠት እና የጽሁፍ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ጥያቄው ከደረሰው ከ፭ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ የመስጠት፤

ሐ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ለወጣላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ይሁንታ የማግኘት፣ የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የማቅረብ እና የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት የማድረግ፤

መ) አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች እና አገልግሎቶች ደህንነታቸውና ጥራታቸው የተጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሠ) በምርቶች ወይም በአገልግሎቶች ላይ በአስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች የገላጭ ጽሁፍ መስፈርት መሰረት መረጃዎችን የመጻፍ፤

ረ) ያመረታቸው፣ ወደ ውጭ ሀገር የላካቸው፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስመጣቸው፣ ያከማቻቸው፣ ወይም ያከፋፈላቸው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለመጨረሻ ተጠቃሚው እስከሚደርሱ ድረስ ያለውን የስርጭት ሁኔታ ሊያሳይ የሚችል

d) Acquire appropriate, ethical and impartial service from the Ministry.

2/ Any Implementer shall have the obligations to:-

a) Allow the inspector, upon verifying his identification card and an authorization letter issued by the Ministry, to enter into the business establishment without any advance notice during and out of regular working hours, conduct Inspection and oversight, take product sample for free at production, storage and transportation facilities, require and acquire any necessary information relating to the inspection;

b) Give relevant information forthwith and provide written explanation not more than five working days from the receipt of such request;

c) Obtain the necessary permit, hold a conformity certificate and affix Ethiopian standards mark on products or services subject to mandatory Ethiopian standards;

d) Ensure that products and Services subject to mandatory Ethiopian standards fulfill quality and safety requirements;

e) Label products or services subject to mandatory Ethiopian standards based on the mandatory standard labeling requirements;

f) Put in place a system which shows the supply chain of products or services subject to mandatory Ethiopian standards that he produced, exported, imported, stored or distributed until

የመረጃ አያያዝ የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፣ ሰነዶች የመያዝ፤ በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማቅረብ፤

ሰ) ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የማክበር።

**፴፪.የኢንስፔክተር ተግባርና ኃላፊነት**

ማንኛውም ኢኒስፔክተር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

፩/ በሀገር መግቢያ እና መውጫ በሮች የገቢና ወጪ ምርቶች ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤

፪/ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ለማስፈጸም በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም የማምረቻ፣ የአገልግሎት መስጫ፣ የማከማቻ፣ የማከፋፈያ ወይም የችርቻሮ ተቋም ወይም ማጓጓዣ ያለ ምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ የመግባት፣ ምርመራ የማካሄድ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ናሙና በነጻ የመውሰድ፣ የማሸግ፣ የላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ ምርቶቹ ለብቻ ተለይተው እንዲቀመጡ የማዘዝ፣ በሕግ አግባብ ምርቶችን የማገድ፣ የመያዝ ወይም ምርቶቹ ወይም ከምርቶቹ ጋር የሚያያዝ ሌላ ነገር ካለበት ቦታ ሳይወጣ ወይም በምንም ዓይነት ሁኔታ ሳይቀየር እንዲከማች የማዘዝ፤

፫/ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟሉ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች በሕገ ወጥ መንገድ ለንግድ አላማ ውለዋል ወይም ሊውሉ ይችላሉ የሚል በቂ ጥርጣሬ ሲኖረው ወደ እነዚህ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ማምረቻ፣ ማከማቻ፣ ማከፋፈያ ወይም ማጓጓዣ የመግባት፣ የመፈተሽ፤ የመመርመር ወይም ስርጭታቸውን የማገድ፤

they reach the end consumer; Keep such records and furnish them upon the request of any regulatory body;

g) Observe and implement the provisions of this Proclamation, Regulation and Directive issued hereunder.

**32. Duties and Responsibilities of the Inspector**

Any inspector shall have duties and responsibilities to:-

1/ Perform regulatory activities on import and export products at entry and exit ports of the country;

2/ Enter into any manufacturing, service, storage, distribution or retailing establishments or transportation facilities at any time without prior notice for the purpose of enforcing this Proclamation, Regulation and Directive issued hereunder, and conduct Inspection, take samples free of charge when necessary, order the seal and detaintion of products until laboratory test results are known, seize products in accordance with the law, order the storage of products without removal or any alteration of another thing related to them;

3/ Enter into and inspect the manufacturing, storage, distribution or transportation facilities and suspend the distribution of products or services that do not comply with mandatory Ethiopian standards where he has sufficient ground to suspect that they have been or may be illegally used for commercial purposes;

CamScanner

፬/ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ፈጻሚዎች፣ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች በተመለከተ እንደ አስፈላጊነቱ ናሙናዎችን፣ ልኬቶችን፣ ፎቶግራፎችን፣ የቪዲዮ ቅጂዎችን ወይም የሰነድ ግልባጮችን ጨምሮ በእነዚህ ሳይወሰን ተቀባይነት ያላቸውን ሌሎች ማስረጃዎች የመሰብሰብ፣ የመያዝ እና ለሚኒስቴሩ የማቅረብ፤

፭/ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ጊዜያቸው በማብቃቱ ወይም ጥቅም ላይ የማይውሉ ሆነው በመገኘታቸው ምክንያት እንዲወገዱ በሚኒስቴሩ ሲወሰን በአግባቡ መወገዳቸውን የመቆጣጠርና መረጃ የመያዝ።

## ፴፫.<u>የኢንስፔክተር ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ኢንስፔክተር፡-

፩/ ሥራውን በሚያከናዉንበት የፈጻሚው የንግድ ድርጅት የኢንስፔክሽን ተግባሩን ከመጀመሩ በፊት ኢንስፔክተር መሆኑን የሚገልጽ ከሚኒስቴሩ የተሰጠውን የመታወቂያ ወረቀት እና ደብዳቤ የማሳየት፤

፪/ የዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ድንጋጌዎች መጣሳቸውን ሲያውቅ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት የማቅረብ፤

፫/ ናሙና ሲወስድ ለፈጻሚው ደረሰኝ ወይም የመረከቢያ ሰነድ የመስጠት፤

፬/ በሥራ አጋጣሚ ያገኘውን ማንኛውንም መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጢር የመያዝ፤

፭/ የበላይ ኃላፊን ሕጋዊ ትዕዛዝ በማክበር በትጋት፣ በታማኝነት፣ በጥንቃቄ እና በተቻለ ፍጥነት ሥራውን የመፈፀም።

4/ Collect and present to the Ministry admissible evidences concerning the Implementer, products or Services subject to mandatory Ethiopian standards including, but not limited to, samples, measurements, photographs, video recordings or copy of records;

5/ Control and keep records of the proper disposal of expired or unusable products or Services subject to mandatory Ethiopian standards upon the decision of the Ministry.

## 33. <u>Obligations of Inspectors</u>

Any inspector shall:-

1/Show his identification card and an authorization letter issued by the Ministry to confirm that he is an inspector before conducting any inspection activity in the business place of the Implementer;

2/ Report to the Ministry the violation of any provisions of this Proclamation, Regulation and Directive issued here under known to him;

3/ Give a receipt or a receiving note to the Implementer where he take sample;

4/ Maintain the confidentiality of any information or document he obtained as a result of his responsibilities;

5/ Discharge his responsibilities with due care, diligence, honesty and timeliness and respect the lawfull orders of higher officials.

CamScanner

፴፬.በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን ያለው አካል ሥልጣንና ተግባር

በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎች በወጣላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ በክልሉ ውስጥ የገበያ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፣ ከሚኒስቴሩ ጋር መረጃ ይለዋወጣል ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚያደርገው ጥናት ላይ ተመስርቶ በሚሰጠው ውክልና መሠረት በክልሉ የፋብሪካ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

፴፭.መዝገብ ስለማደራጀት

ሚኒስቴሩ ለማንኛውም ፈጻሚ የሰጠውን ይሁንታ በተመለከተ የተሟላ እና ትክክለኛ ዝርዝር የያዘ እና ለሕዝብ ክፍት የሆነ መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

ክፍል ሰባት

ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እና ስለ ወንጀል ቅጣት

፴፮.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩/ ሚኒስቴሩ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የተመረቱ፣ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ፣ በገበያ ላይ ያሉ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟሉ ስለመሆናቸው በቂ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር እንደነገሩ አግባብነት በላብራቶሪ ፍተሻ ወይም በኢንስፔክሽን እስኪረጋገጥ ድረስ ፈጻሚው በራሱ ይዞታ ሥር እንዲያቆያቸው ወይም አገልግሎት መስጠቱን እንዲያቋርጥ ትዕዛዝ የመስጠት፣

34.Powers and Duties of Regional Trade Offices

Anybody authorized to administer trade in a Region shall:-

1/ Conduct market surveillance and inspection activities on products and services subject to mandatory Ethiopian standards and share information with the Ministry.

2/ Carry out factory surveillance when delegated by the Ministry based on the study periodically conducted.

35. Keeping a Register

The Ministry shall keep a register open to the public showing complete, accurate and detailed data regarding the permit issued to any Implementer.

PART SEVEN

ADMINSTRATIVE MEASURES AND PENALTIES

36. Administrative Measures

1/ The Ministry may:-

a) Order the Implementer to hold products under his possession or terminate the provision of services for a specified period until their compliance is certified by a laboratory test or inspection, as appropriate, when it has a reasonable ground to suspect that products or Services in the market do not fulfill the mandatory Ethiopian Standards;

CamScanner

ለ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት እንደ ነገሩ አግባብነት ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የማገድ፣ በባለቤቱ ወጪ እንዲወገዱ ወይም ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የማድረግ፣ ስርጭታቸው እንዲቋረጥ ወይም ከገበያ እንዲሰበሰቡ የማዘዝ፣ የማሸግ፣ የመውረስ ወይም ሌሎች ህጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የማድረግ፤

ሐ) በሀገር ውስጥ የተመረቱ፣ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ፣ ለገበያ የቀረቡ ወይም ወደ ውጪ ሀገር የሚላኩ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟሉ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ለፈጻሚው የሚሰጠውን ይሁንታ የመከልከል ወይም የሰጠውን ይሁንታ የማገድ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው ደንብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለክልከላው ወይም ለእገዳው ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ማስተካከያ ካልተደረገ ይሁንታውን የመሠረዝ፡፡

፪/ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ከምልክት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተላልፎ በተገኘ ማንኛውም ፈጻሚ ላይ እንደነገሩ አግባብነት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የደረጃ ምልክት ፈቃድ የማገድ ወይም የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

b) Bar products or services specified under sub-article (a) above from entering the country, dispose them at the expense of the owner or re-export them to the country of origin, suspend their distribution, decide their confiscation or cause other legal measures to be taken in accordance with the Regulation issued hereunder where it is confirmed that they are not in compliance with the requirements of mandatory Ethiopian standards;

c) Refuse or suspend a permit when it has been satisfied that products or Services locally produced, imported, provided for sale or those ready for export are not in compliance with the mandatory Ethiopian standards and revoke such permit if corrective measures are not taken by the implementer within the period specified in the Regulation issued hereunder.

2/ The Standards Institute shall take administrative measures including written warning, suspension and revocation of the authorization of Ethiopian standards mark, as appropriate, on any implementer who violates the provision of this Proclamation, Regulation and Directive issued hereunder relating to standard mark.

CamScanner

፫/ በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ በተሰጠው ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፡-

ሀ) የተመረቱ ወይም በገበያ ላይ ያሉ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟሉ ስለመሆናቸው በቂ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር እንደነገሩ አግባብነት በላብላቶሪ ፍተሻ ወይም በኢንስፔክሽን እስኪረጋገጥ ድረስ ፈጻሚው በራሱ ይዞታ ሥር እንዲያቆያቸው ወይም አገልግሎት መስጠቱን እንዲያቋርጥ ትዕዛዝ የመስጠት፤

ለ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን የማያሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በሚወጣ ደንብ መሠረት እንደነገሩ አግባብነት በባለቤቱ ወጪ እንዲወገዱ፣ስርጭታቸው እንዲቋረጥ ወይም ከገበያ እንዲሰበሰቡ የማዘዝ፣የማሸግ፣የመውረስ ወይም ሌሎች ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የማድረግ፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ፣ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት እና በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ተገቢውን ጥንቃቄ በመውሰድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) መሠረት የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በሀገሪቱ ሰፊ ሽፋን ባለው የመገናኛ ብዙሐን ለሕዝብ መግለጽ አለባቸው፡፡

3/ A body authorized to administer trade in a region in accordance with Article 34 of this Proclamation shall take the following administrative measures:-

a) Order the Implementer to hold products under his possession or terminate the provision of services for a specified period until their compliance is certified by a laboratory test or inspection, as appropriate, when it has a reasonable ground to suspect that products or Services in the market do not fulfill the mandatory Ethiopian standards;

b) Dispose products or terminate services specified under Sub-Article (a) above at the expense of the owner, suspend their distribution, decide their confiscation or cause other legal measures to be taken in accordance with the Regulation issued hereunder where it is confirmed that they are not in compliance with the requirements of mandatory Ethiopian standards.

4/ The Ministry , the Standards Institute or the body authorized to administer trade in a region shall, in due care, notify the public the measures taken pursuant to Sub-Article (1), (2) and (3) of this Article through mass media with wider coverage in the country.

CamScanner

**፴፯.ቅሬታ ስለማቅረብ**

፩/ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በሚሸፈን ማናቸውም ጉዳይ ላይ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ በተሠጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔ በተሰጠ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደነገሩ አግባብነት ለሚኒስቴሩ፣ለደረጃዎች ኢንስቲትዩት ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን ለተሰጠው አካል የበላይ ኃላፊ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ የሚኒስቴሩ ፣ የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል የበላይ ኃላፊ ቅሬታ በቀረበ በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ የሚኒስቴሩ ፣የደረጃዎች ኢንስቲትዩት ወይም በክልል ንግድን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ያልተሰጠው ማንኛውም ሰው በሠላሳ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፴፰.የተከለከሉ ድርጊቶች**

አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

፩/ በደረጃዎች ኢንስቲትዩት ያልጸደቀ ወይም የተሻረ ደረጃን እንደ ኢትዮጵያ ደረጃ አድርጎ መጠቀም፤

**37. Grievance**

1/ Any person who is aggrieved with the decision of any concerned official regarding matters covered in this Proclamation, Regulation and Directive issued here under may lodge his complaint in writing to the Head of the Ministry ,the Standards Institute or the body authorized to administer trade in a region, as appropriate, within Ten working days from the rendering of such decision.

2/ The Head of the Ministry, the Standards Institute or the body authorized to administer trade in a region shall notify his decision in writing to the aggrieved person within fifteen working days from the receipt of the complaint.

3/ The complaint may lodge his complaint to the competent Court within Thirty days from the rendering of the decision if he is aggrieved by the decision of the Head of the Ministry, the Standards Institute or the body authorized to administer trade in a region or if he has not received a written decision within the time limit specified under Sub-Article of this Article.

**38. Prohibited Acts**

Without prejudice to other prohibitions provided in this Proclamation and other appropriate laws, the following acts are prohibited:-

1/ Using a standard which is not approved or withdrawn by the Standards Institute;

CamScanner

፪/ ይሁንታ ሳያገኝ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ማምረት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ከውጪ ሀገር ማስመጣት፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ማሰራጨት ወይም ለገበያ ማቅረብ፤

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ይሁንታ ወይም ውቅና ካለው የተስማሚነት ምዘና አካል ያገኘውን የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ወይም እነዚህን ሰነዶች ለመቀበል መብት ሳይኖረው መቀበልና መገልገል፤

፬/ ድርጊቱ በሰው፣ በእንስሳት ወይም በእጽዋት ጤንነት ወይም ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ቢሆንም ባይሆንም አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን ምርቶች ከባእድ ነገር ጋር መደባለቅ፣ አስመስሎ መስራት ወይም ደረጃቸውን የማያሟሉ እንዲሆኑ ማድረግ፤

፭/ ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት ተገቢውን የመጠቀም ፈቃድ ሳያገኝ በኢትዮጵያ የደረጃ ምልክት መጠቀም፣ ያልታደሰ ወይም የተሰረዘ ምልክት መጠቀም፣ ምልክቱን ባልተፈቀደለት ምርት ወይም አገልግሎት ላይ መጠቀም፣ ምልክት ሳያደርግ አስገዳጅ ደረጃ የወጣለትን ምርት ወይም አገልግሎት ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ከውጭ ሀገር ማስመጣት፣ ማሰራጨት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ ማስተዋወቅ፣ ሕጋዊ ያልሆነ ምልክት ሕጋዊ አስመስሎ መጠቀም ወይም በሕገወጥ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ፤

2/ Producing, exporting, importing, storing, transporting, distributing or supplying to the market products or Services subject to mandatory Ethiopian standards without obtaining the necessary permit;

3/ Transferring a permit obtained pursuant to this Proclamation or a conformity assessment certificate issued by a recognized conformity assessment body to a third party or receiving and using such documents without having the right to do so;

4/ Committing adulteration of products subject to mandatory Ethiopian standards and causing such products to be counterfeited and substandard irrespective of the fact that they cause harm on the health or safety of human beings, animal or plants;

5/ Using Ethiopian standards mark without obtaining the necessary authorization from the Standards Institute, using an expired or revoked standard mark, using the mark for products or Services to which the mark is not allowed, exporting, importing, distributing, supplying or promoting products or Services subject to mandatory Ethiopian standards without affixing an Ethiopian Standard Mark, using an illegal standard mark as legal, or transferring the mark illegally to another person;

CS CamScanner

፮/የአንድን ምርት ወይም አገልግሎት ደረጃን በተመለከተ የተጭበረበረ ወይም ሀሰተኛ የተስማሚነት ምዘና ማረጋገጫ ማቅረብ ወይም መስጠት ወይም የምርቶችን አይነት በመግለጫ ጽሑፍ ላይ ሳይገልጽ ወይም በሚያሳስት ሁኔታ ለገበያ ማቅረብ፡፡

**፴፱.ስለቅጣት**

ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው፡-

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን የተከለከሉ ድርጊቶች ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ሀያ አምስት ሺህ እስከ ሀምሳ ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) የተመለከቱትን የተከለከሉ ድርጊቶች ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ከስድስት ወር እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር ሀምሳ ሺ. እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከቱትን የተከለከሉ ድርጊቶች ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ከሦስት ዓመት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አንድ መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

6/Producing or issuing false conformity certificate for the standards of products or services or supplying products without labeling or in a misleading manner.

**39. Penalty**

In addition to the confiscation of the regulated product:-

1/ Any person who violates Article 38 Sub-Article (1) of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment from One year to Five years and fine from birr Twenty Five Thousand to Fifty Thousand ;

2/ Any person who violates Article 38 Sub-Article (2) or (3) of this Proclamation shall be punished with simple imprisonment from six months to Three years and fine from birr Fifty Thousand to One Hundred Thousand;

3/ Any person who violates article 38 Sub-Article (4) of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment from Three years to Seven years and fine from birr one hundred thousand to two hundred thousand;

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም (፮) የተመለከቱትን የተከለከሉ ድርጊቶች ፈጽሞ የተገኘ እንደሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አንድ መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ የተመለከቱት የተከለከሉ ድርጊቶች የሕግ ሰውነት ባለው አካል የተፈጸሙ በሆነ ጊዜ ከብር አንድ መቶ ሺህ እስከ አምስት መቶ ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል::

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ ማንኛውም ይሁንታ፣ የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና የኢትዮጵያ ደረጃ ምልክት ፈቃድ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተሰጠ ይቆጠራል::

፪/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተመረቱ ወይም በመጓጓዝ ሂደት ላይ የሚገኙ ምርቶች እና አገልግሎቶች በነባሩ ሕግ መሠረት ይስተናገዳሉ::

**፵፩.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በመፈጸምና በማስፈጸም ሂደት የመተባበር ግዴታ አለበት::

**፵፪.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል::

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን በአግባቡ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

4/ Any Person who violates article 38 Sub-Article (5) or (6) of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment from one year to five years and fine from birr One Hundred Thousand to Two Hundred Thousand;

5/ A juridical person who violates the provisions of Article 38 of this Proclamation shall be fined from Birr one Hundred Thousand to Five Hundred Thousand.

## PART EIGHT
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**40. Transitory Provisions**

1/ Any permit, conformity assessment certificate or Ethiopian standard mark granted before the coming into force of this Proclamation shall be considered to be issued under this Proclamation.

2/ Products and Services produced or being transported before the coming in to effect of this Proclamation shall be subject to the existing law.

**41. Duty to Cooperate**

Any person shall have the duty to cooperate for the enforcement of this Proclamation, Regulation and Directive issued hereunder.

**42. Power to Issue Regulation and Directive**

1/The Council of Ministers may issue Regulation necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/The Ministry may issue Directive necessary for the proper implementation of this Proclamation and Regulation issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

CamScanner

## ፵፫.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፫/፪ሺ፲ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## ፵፬.<u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፫/፪ሺ፲ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል።

## ፵፭.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 43. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/The Ethiopian Standards Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 193/2010 is hereby repealed.

2/ No Proclamation, Regulation, Directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters covered by this Proclamation.

## 44. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>

The rights and obligations of the Ethiopian Standards Agency established in accordance with the Council of Ministers Regulation No.193/2010 is hereby transferred to the Institute of Ethiopian Standards established pursuant to this Proclamation.

## 45.<u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this Day of October 23th, 2024**

**SAHALE -WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

CamScanner